

በ: ሺርሊ ፕራንቶ
ምሳሌዎች: ዴይቪድ ዎከር
הוֹצָאָה: תכלת
የእድሜ ክልል: ታዳጊዎች

קְרִיאָה

ለቤተሰባዊ ንባብ የሚሆን ጠቃሚ ምክር - ከመጽሃፉ ወደ ሕይዎት
መጽሃፍት ፈታኝ ሁኔታዎችን ለመቋቋም ይረዳሉ። ታዳጊዎች በመጽሃፍቱ ውስጥ ካሉ ገፀ-ባህሪያት ጋር ይተዋወቃሉ። በውጤቱም በመጽሃፍቱ ውስጥ እንዲሁም በሕይወታቸው ውስጥ ስላሉት ስሜቶች፣ ባህሪዎችና ተግዳሮቶች ይማራሉ። በመጽሐፉ ውስጥ ከቀረቡት ጋር በሚመሳሰሉ ሁኔታዎች ውስጥ ታዳጊዎችን የመጽሐፉን ጀግኖች ለማስታወስና መነሳሻን እንዲስሉ በተመሳሳይ መንገድ እንዲሠሩ ሀሳብ መስጠት ትችላላችሁ – "ምናልባት አግዳሚ ወንበር ላይ "ትንሽ ልንንቀሳቀስና ከመጽሐፉ ውስጥ እንዳሉት ድቦች ለጓደኛ ቦታ እንሰጥ ይሆናል።

שִׂיחָה

?ታሪኩ ላይ ምን እየሆነ ነው
በመጽሐፉ ውስጥ ስላለው ክስተት ከታዳጊዎች ጋር መነጋገር ትችላላችሁ – ድቦች ምን ችግር አጋጥሟቸዋል? ለምን ድቡ የሚቀመጥበት ቦታ አልነበረውም? ሌሎቹ ድቦች ምን አደረጉ? እንዲሁም ከታሪኩ የሚነሱትን ስሜቶች መጥቀስ ትችላላችሁ -ቴዲ ድብ ቦታ በሌለው ጊዜ ምን ተሰማው? ተደስቶ፣ አዝኖ ወይም ምናልባት ተገርሞ ወይስ ግራ ?ተጋብቶ ነበር

סִרְטוֹנִים

QR ኮድ - በድቦች ጨዋታ

ታሪኩን ማቅረብ ትፈልጋላችሁ? – ኮዱን ስካን በማድረግ የድብ ገጸ ባህሪዎችን ማተም፣ ቀለም መቀባትና አንድ ላይ ማሳየት ትችላላችሁ!

מִשְׂחָק

በምስሎች ማንበብ

በምስሎቹ አማካኝነት መማር፣ መጫወትና መደሰት ትችላላችሁ። በእያንዳንዱ ጊዜ በምስሎቹ ውስጥ የተለያዩ ዝርዝሮችን መፈለግ ትችላላችሁ – ሮዝ ቴዲ ድብ የት አለ? ባለነጠብጣቡ ድብ የት አለ? ትልቁ ድብና ትንሽ ድብ የት አሉ?

ሚናዎችን በመቀያየር ታዳጊዎቹ በምስሉ ላይ እቃዎችን እንድትፈልጉ እንዲጋብዙ ማድረግ ትችላላችሁ።

“

הַשְׁרָאָה

ፒንተረስት

ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎችና ሀሳቦች በ”ፒጃማ ቤተ መጻህፍት ለትናንሽ ልጆች” ላይ እየጠበቁዎት ነው።

כְּלָלִי

እንደ ድብ

መጽሐፉን በማገላበጥ ልክ በምስሉ ላይ እንዳለው በእያንዳንዱ ጊዜ በተለያየ ገጽ ላይ በማቆም ድቦችን መመልከትና እንቅስቃሴያቸውን፣ የተቀመጡበትን መንገድ ብሎም የፊት ገጽታን ለመምሰል መሞከር ትችላላችሁ።